# <u>የመጨረሻው ደወል</u> !

(አሥራደው ከፈረንሳይ)



ኳ! ኳ! ኳ!  ይላል፤

በማርያም ደጃፍ - በገብርኤል፤
በጎርጊስ ደጅ - በሩፋኤል፤
በጨርቆስ ደጃፍ - በአማኑኤል፤
በተክልዬ - በሚካኤል፤

ኳ!  ኳ!  ኳ!  እያለ፤
የመጨረሻው ደወል ተደወለ፤
አትንበርከክ በቃ !
ቆመህ የጴጥሮስን ሞት ሙት አለ።

ስደት አገር አሟጦ - ሃዘን አጉብጦ ፤
ችጋር አጥንትህን ግጦ - ፍርሃት አንቀጥቅጦ ፤
ድህነት አፍጥጦ - በደል አንፈራጦ ፤
አይግዛህ ይበቃል፤
የአያት የቅድም አያቶችህ ቃል፤
እንቢኝ ነው ደጉ - እንቢኝ ይበልጣል።

ይዩት  ድፍረትህን !
ይወቁት ኩራትህን !
አትበርከክ  ይበቃል፤
እንቢኝ በል ! - እምቢኝ ይሻላል።

የልጆችህ አንገት በበረሃ ሲቀጭ ፤
የአያት የቅድም አያቶችህ አጽም ሲንቀጫቀጭ ፤
ተንበርክከህ ሳይሆን አጎንብሰህ ፤
የጀግኖችን ሞት ሙት ቆመህ ።
የአያት የቅድም አያቶችህ ወጉ ፤
እምቢኝ ይሻላል - አሻፈረኝ! ነው ደጉ ።

ሞት በገዛ እጁ አፈረ፤
እስላምና ክርስቲያኑ ተባበረ፤
በኢትዮጵያ ምድር አብሮ እንደኖረ፤
በአንድነት ቆሞ መሞት ጀመረ።

ቆመህ የጴጥሮስን ሞት ሙት ፤
አትፍረክረክ ጽና በዕምነት !
የጀግና ልጅ ጀግና መሆንክን ይወቁት፤
ለጨቋኞች አትንበርከክ - ቁም ለነፃነት።

እነሆ ኳ! ኳ! ኳ! ይላል፤
የመጨረሻው ደወል ተደውሏል፤
የበደል ፍጻሜው ይሆናል ።
ኳ! ኳ! ..........ኳ !!!!!

ቆመህ የጴጥሮስን ሞት ሙት፤ የሚለው ሃረግ
በ 5 ዓመቱ የጣሊያን ወረራ ወቅት፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለጣሊያን ወረራ እንቢኝ እንዲልና፤ በጭራሽ እንዳይንበረከክ ጥሪ በማድረጋቸው፤ በጣሊያኖች ጭካኔ የተረሸኑት ኢትዮጵያዊው አቡነ ጴጥሮስን ለማስታወስ መሆኑን አንባቢ ይገነዘብ ዘንድ እወዳለሁ።

በአገር ውስጥ፤ በደቡብ አፍርካ፤ በሊቢያ፤በየመንና በየዓረብ አገራቱ፤ በአደጋ ላይ ሆነው ለሚንገላቱና፤ ለሞት ለተዳረጉ ወገኖቻችን መታሰቢያ።

ግንቦት 2/ 2007 ዓ.ም. (May 10/2015)